## ኦሮሞ ፓለቲካና የደምቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እጣ ፋንታ

## በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተ ልብ ወለድ

## ክፍል ፯ የየእኛ ማስታወሻ፣ ካለፈው የቀጠለ

ስለአዴፓ ዘላለማዊ አስጠቂነት ስታሰላስል፣ አሁን ለውጥ የተባለው ከመጣ በኋላ ደግሞ እንደ ወያኔ ሁሉ ታሪካዊ እድል ያገኙት የኦሮሞ ባለስልጣናት በትክክል በቅንነትና በእኩልነት ማስተዳደር ሲገባቸው ከወያኔ በከፋ ሁሉንም ለኦሮሞ የሚል አጀንዳ ጭካኔ አላብሶ ከፍተኛ ወንጀል እያስፈፀማቸው ነው፣ አለች የእኛ ከሰመጠችበት ጥልቅ ሀሳብ እየወጣች። ጫልቱ አንዳንድ ቀን ሲከፋሽ ስሜትሽን ታወጭበታለሽ ብላ የገዛችላትን ዳጎስ ያለ ምንም ያልተፃፈበት ደብተር እያገላበጠች።

የእኛ በውስጧ የሚተረማመሰውንና መልስ ያላገኘችለትን የወቅቱ የኢትዮጵያ አስፈሪ ፓለቲካና የአማራ ህዝብ መከራ በፅሁፍ ለማስፈር አሰባለች ። ነገር ግን ብዙ ግራ ያጋባት በጭንቅላቷ የሚተረማመስ ነገር ቢኖርም የትኛውን ለብዕር እንደምታውለው ለመምረጥ ተቸግራለች ። መጀመሪያ አካባቢ ለመፃፍ የምታስበው ስለእሷና ስለደምቢ ዶሎ ተማሪዎች መከራ ነበር። አሁን አሁን ግን በየቀኑ በየሰዓቱ አዳዲስ ጉድ እየተሰማ ስለሆነ፣ ሁሌም የመከራ ቀላል የለውም ብትልም፣ የትኛውን መከራ አንስታ የትኛውን እንደምትተወው ለመምረጥ ተቸግራለች። አዳዲስ ለጆሮ የሚዘገንን ግድያ፣ ከአሁን በፊት በታሪክ እንኳዋን ሰምታው የማታውቀው አሰቃቂ የአገዳደል አይነት በኦሮሞና በጉሙዝ ፅንፈኞች እየተፈፀመ ነው።

ጠቅላይ ሚንስትር አብይ ስልጣን ከያዘ ጀምሮ በርካታ አዲስ አበባውያንና በስዲስ አበባ ዙሪያ ያሉ ከኦሮሞ ያልተወለዱ ሰዎችን ቤታቸውን በላያቸው ላይ በግሬደር እያፈረሱ ቤት አልባ አድርገዋቸዋል።

አዲስ አበባ ላይ የቤት ችግር ስላለ ነዋሪው ይኽን ችግር ለመቅረፍ፣ ብዙ ሺ ህዝብ መንግስትን አምነው አንጀታቸውን አስረው፣ ከልጆቻቸው ጉሮሮ ነጥቀው፣ ያሰሩት የኮንዶሚኒየም ቤት በኦሮሞ ባለስልጣን እየተዘረፈ የአዲስ አበባ ነዋሪ ላልሆኑ ኦሮሞዎች በተረኝነት መንፈስ የተሾመው ከንቲባ ታከለ ኡማ አድሏል። የመሬት ወረራውም ተባብሷል።

በመሃል አዲስ አበባ ሳይቀር የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ የያዘ ሰው ሲቀማና ሲንገላታ በአደባባይ ታይቷል። አዲስ ስበባና መከራዋ ሲሰማ እነእስክንድር ነጋንና ባልዳራስ እንዲሁም እንደ ልደቱ አያሌው አይነት ፓለቲከኞች ለእስር መዳረግ ለውጡ እንዴት ወደተረኝነት እንደተለወጠ ማሳያ ነው ብላ ታምናለች ።

የኦሮሞው ፕሬዚዳንት ሽመልስ አብዲሳ እንዴት አማራና አማርኛን እያጠፉና እያዳከሙ ውጤታማ እንደሆኑ፣ ለዚህም መርሃግብር ማስፈፀሚያ ማደናገርና ማታለልን ቅድሚያ ሰጥተው እንደሚጠቀሙ የተናገረውን በአማርኛ ተተርጉሞ ሰምታ ስትገረም ነበር። በሻሸመኔ፣ በአርሲ፣ በዝዋይ፣ አጋርፋ፣ አሳሳ፣ ዴራ ወዘተ በአማራና በኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች ላይ የተደረገ አሳዛኝ ጭፍጨፋ ስታይና ስትሰማ የሽመልስ አብዲሳ ንግግር ፍሬ አፈራ ብላለች።

አሁንም የሽመልስ አብዲሳን መርሃ ግብር የሚያስቀጥል ስራ ነው ብላ ያመነችው የሰሞኑ፣ በጉምዝ አማካኝነት ትኩረቱን በአማራ፣ በአገው ተወላጅና በኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች ላይ ያደረገውን ጭፍጨፋ ስትሰማ ነበር። እንደየእኛ መረዳት ከሆነ ቤኒሻንጉል ጉምዝ ላይ የሚደረገው የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ በኦሮሙማ ፅንፈኝነት የተለከፈው የኦዴፓው ሽመልስ እንዳለው፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ኦሮሞኛ 37 % አደገ ያለውን ለማጠናከር ከስግብግብነት የመጣ የጭካኔ የጭፍጨፋ ርምጃ ነው። ጉምዞች እንደገዳዩ ቀስታቸው እነሱም የነሽመልስ አብዲሳ የመግደያ መሳሪያ ቀስት ናቸው።

የእኛ በደሉና የተበዳዩ ትዕግስት አልተመጣጠነላትም። በኦሮሞ ፓለቲካ ስንት ሰው ለእስር ተዳረገ? ስንት አማራና የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች ታረዱ? ስንት ባንክ ቤቶች ተዘረፉ? ሰው ተዘቅዝቆ ታስሮ ተገደለ! በግፍ የተገደለ ሰው አስከሬን ተቆራረጠ፣ ተጎተተ! ተቃጠለ! ነፍሰጡሮችና ህፃናት ታረዱ፣ የወንዶች ብልት የሴቶች ጡት ተቆረጠ፣ አብያተክርስቲያናት ተቃጠሉ፣ ሰዎች በማንነታቸውና በእምነታቸው ተፈርጀው ተፈጁ፣ የስንቶቹ ቤት ንብረታቸው ተቃጠለ? እኛስ የአማራ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በመሆናችን አይደል ታፍነን ተወስደን ወድቀን ከቀረን አንድ አመት ሊሞላን ነው። አሁን ኢትዮጵያ አለች ይባላል? ኢትዮጵያዊስ አለሁ ይላል? እያለች የምታነሳው የምትጥለው ነገር አጥታና ስትጨነቅ በልጅነቷ አያቷ የሚሉትን አስታወሰች።

እናት አባት ቢሞት በአገር ይለቀሳል

እህት ወንድም ቢሞት በአገር ይለቀሳል

አገር የሞተ እንደሁ ወዴት ይደረሳል

እያሉ አያቷ ስለሀገር ክብርና ጥቅም የሚገልፁበት ግጥም ፋይዳ እንዳለው የገባት በዚህ በችግሯ ሰዓት ነው። እሷም እማስታወሻዋ ላይ የአያቷን ግጥምና የራሷን ከታች ያለውን ግጥም አሰፈረች።

አገሬ አትሙች እኔ ልሙትልሽ

ኢትዮጵያ አትፍረሽ እኔ ልፍረስልሽ

በጣም ተዋርደናል ገና በህመምሽ ።

የቀን ጅብ መፈንጫ አቅመቢስ ሆንልሽ

ክፍል ፲. ፩ የየእኛ ማስታወሻ ይቀጥላል፡-

ዘውዲቱ የማነ

2020-09-25